Persee

André Caquot

Histoire amharique de Grāñ et des Gallas

In: Annales d'Ethiopie. Volume 2, année 1957. pp. 123-143.

Citer ce document / Cite this document :

Caquot André. Histoire amharique de Grāñ et des Gallas. In: Annales d'Ethiopie. Volume 2, année 1957. pp. 123-143.

doi : 10.3406/ethio.1957.1262

http://www.persee.fr/web/revues/home/prescript/article/ethio_0066-2127_1957_num_2_1_1262

BY: creative commons

HISTOIRE AMHARIQUE DE GRĀÑ ET DES GALLAS

PAR

A. CAQUOT

Persée creative commons

Ce récit traditionnel sur l'origine du peuple galla et sur les causes de l'invasion de Grāñ se rattache étroitement au *dersāna Rāgu'ēl* étudié plus haut. Dans le *tārika nagast* d'Addis Ababa dont le texte est pris ici comme base (manuscrit *B*), la vision de l'Empereur Lebna Dengel est placée dans la narration des événements du XVI^e^ siècle qui mirent l'Éthiopie à deux doigts de sa perte. Il s'agit d'expliquer les malheurs inouïs qui s'abattirent sur la nation. Pour l'auteur de ces textes, sans aucun doute un clerc ou un prêtre, comme pour les rédacteurs des *Chroniques* de l'Ancien Testament, les malheurs du peuple ont été provoqués par le péché du roi. Lebna Dengel est représenté comme coupable d'avoir toléré et encouragé par son exemple des pratiques païennes : ici consommation du tabac, joutes équestres. Il est aussi coupable de s'être laissé aller à l'orgueil, appelant ainsi la venue de Grāñ, véritable fléau de Dieu.

Les pratiques reprochées à Lebna Dengel sont attribuées à l'imitation des Gallas, on est donc conduit à installer ce peuple en Éthiopie bien avant le règne de Lebna Dengel. Noter cependant que le texte n'hésite pas à se contredire à ce sujet et à parler des Gallas comme de la postérité de Grāñ, ce qui correspond à peu près à la date de leur apparition. Le manuscrit *C*, dont je dois la connaissance à l'amitié d'*Ato* Asafa Abbeyé Joseph, fixe au règne de Sarṣa Dengel l'épisode de la rencontre des premiers parents des Gallas, alors que le manuscrit *B* parle du temps d'Amda Ṣeyon. On a là un témoin de ces spéculations fantastiques sur un peuple dont la venue terrifiante d'abord, puis la place qu'ils ont prise dans l'État au temps des rois de Gondar, ne pouvaient manquer d'être interprétées comme des « signes » par les gardiens de la culture traditionnelle et de l'histoire d'Éthiopie. Spéculations qui ont pu apparaître en même temps que les Gallas eux-mêmes. Cependant, à la fin du XVI^e^ siècle, le moine Bāḥrey, auteur d'un *zēnāhu lagāllā* [1], fait preuve en

[1] Éditions A. W. SCHLEICHER, *Geschichte der Galla,* Berlin, 1893; I. GUIDI, *Historia gentis Galla, Corpus scriptorum christianorum orientalium, Aeth.*, ser. altera, III, p. 231 et suiv., traduction p. 193 et suiv., Paris, 1907; traduction dans C. F. BECKINGHAM et G. W. B. HUNTINGFORD, *Some Records of Ethiopia,* Londres, Hakluyt Sty., 1954.

étudiant ce peuple d'un véritable sens historique et son témoignage est encore retenu par les ethnologues [1]. Notre texte, lui, est moins soucieux de décrire les Gallas que de donner à telle ou telle de leurs coutumes ou de leurs attitudes une étiologie purement légendaire et de présenter leurs mœurs comme une sorte de quintessence du paganisme. Il est difficile de fixer à de telles spéculations une origine dans le temps : elles ont pu longtemps circuler oralement. Les deux textes du XIX^{e} siècle publiés par I. Guidi [2] représentent une version courte de la légende. On la retrouve, avec moins de détails, dans la *Chronique du règne de Ménélik II* de Gabra Sellāsē [3]. *Ato* Aṭmē dans son *Histoire* (inédite) *des Gallas*, la rattache comme le *dersāna Rāgu'ēl* au mystérieux livre qu'une *wayzaro* Agāyā fit venir du lac Zwāy pour le montrer à l'Empereur Susenyos; sa laborieuse réfutation souligne le caractère légendaire du récit dont il fait une invention de prêtres désireux de calomnier le pouvoir impérial. De son côté, l'*alaqā* Tāyyē dépend plus étroitement de Bāḥrey, bien que certains détails de notre texte apparaissent dans le court chapitre qu'il consacre au peuple galla [4].

La légende de Grāñ répond à des préoccupations du même ordre. On entend expliquer les succès foudroyants du conquérant musulman d'une part en en faisant l'instrument du châtiment divin, pour punir l'infidélité et l'orgueil de Lebna Dengel, d'autre part en donnant à son action un mobile personnel : le désir de venger son père tué par les moines éthiopiens en massacrant tous ceux-ci. Conti Rossini a relevé une légende tigréenne semblable à celle que nous transmet le texte amharique [5].

ታሪክ ፡ ዘጋላ

በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩አምላክ ። ንጽሕፍ ፡ መጽሐፈ ፡ ታሪክ ፡ ዘጋላ ፡ ወራእየ ፡ ዘርአየ ፡ ንጉሥነ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘርአየ ፡ በእንተ ፡ ሀገሩ ፡ ከመ ፡ ትትኰነን ፡ በእደ ፡ አረሚ ፡ ተንባላት ። ጸሐፍነ ፡ ከመ ፡ ያአምሩ ፡ ደቂቅነ ፡ ለዘይመጽእ ፡ ትውልድ ፡ በደኃሪ ፡ መዋዕል ፡ ከመ ፡ ኢይክሐዱ ፡ ሃይማኖተ ፡ በእንተ ፡ ተኰንኖቶሙ ፡ በእደ ፡ አረሚ ። ኃይለ ፡ ጸሎታ ፡ ለአመ ፡ ብርሃን ፡ ይዕቀበ ፡ ለገብረ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ተክለ ፡ ወልድ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

[1] Voir C. F. Beckingham et G. W. B. Huntingford, p. xxxvi.
[2] *Leggende storiche di Abissinia*, *Rivista degli studi orientali*, I, 1907, p. 5-30.
[3] Paris, 1930, p. 39-53.
[4] *Ya'Ityopyā ḥezb tārik*, Asmara, 1927, p. 35-37.
[5] *Note etiopiche, II Leggende tigray*, in *Giornale della Società asiatica italiana*, X, 1897, p. 150-153.

እነሆ ፡[1] በአፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ረኃብ ፡ ሆነ ። እጨጌ ፡ ፊልጶስ ፡ በሃይማኖት ፡ የተነሣ ፡ ሀገራችንን ፡ ረግመውት ፡ ነበር ። ችጋር ፡ ሆነ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ የንጉሡ ፡ እኅት ፡ ቸግሩት ፡ በፈጠጋር ፡ ነበረች ። አዝማች ፡ እንድርያስ ፡ የሚሉት ፡ የዳወሮና ፡ የከተታ ፡ መኰንን ፡ ነበር ። እሱም ፡ ዘመቻ ፡ ዘመተና ፡ ተጥቂር ፡ ምድር ፡ ላሎ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ማረከ ። የተማረከ ፡ ሰው ፡ ባሪ ፡ ይባል ፡ ነበር ። ያችም ፡ ወይዘሮ ፡ ቢቸግራት ፡ ላሎ ፡ አቤላም ፡ ነበር ፡ ወተት ፡ ያጠጣኛል ፡ ብላ ፡ ሄደች ። እሱም ፡ የቅቤ ፡ ንፍሮ ፡ አበላ ።[1] የቅቤ ፡ ንፍሮ ፡ ማለት ፡ መልሰ ፡ መልሰ ፡ ፱ጊዜ ፡ ቢያነጥሩት ፡ እንደ ፡ አሸዋ ፡ ይሆናል ።

እሷንም ፡ ሚስት ፡ አደረጋት ። ፬ወንዶች ፡ ፫ሴቶች ፡ ወለደችለት ። የወን ዶች ፡ ስም ፡ ከረዩ ፡ ቱለማ ፡ ሜጫ ፡ ወሎ ፡ ይባላሉ ። የሴቶች ፡ ስም ፡ አልከ ፡ ዱረቲ ፡ አያንቱ ፡ ይባላሉ ።[2] ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ሞቱ ። ልጃቸው ፡ አፄ ፡ ሰይፈ ፡ አርዕድ ፡ ነገሡ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ የላሎ ፡ ልጆች ፡ የሰው ፡ ከብት ፡ እያረዱ ፡ ይበሉ ፡ ዝ'መር ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ ተሰብስበ ፡ አቤት ፡ አቤት ፡ አለ ። አዝማች ፡ እንድርያስም ፡ ጌታቸው ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ልጆ ችህን ፡ ይዘህ ፡ ና ፡ ብሎ ፡ ላከበት ። ላሎም ፡ ይኸን ፡ መልእክት ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ገበቶ ፡ ሄደ ። ይኸም ፡ ገበቶ ፡ ጠንቋይ ፡ ነበር ፡ በሀገረ ፡ ከተታ ፡ ወግልያ ፡ የሚባል ፡ የሚስበው ፡ ጋኔን ፡ ነበረው ። የጋኔኑም ፡ እናት ፡ ስሟ ፡ ኩርቢት ፡ ትባል ፡ ነበር ። አባቱ ፡ ግን ፡ እንደኛ ፡ ዘርአ ፡ አዳም ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ላሎ ፡ ሄደ ፡ ያንን ፡ ጠንቋይ ፡ ሲለው ፡ ምን ፡ ባደርግ ፡ ይሻለኛል ።[2] እነዚህ ፡ ልጆች ፡ የሰው ፡ ከብት ፡ ማረዳቸው ፡ እውነት ፡ ነው ። ከአዝማች ፡ እንድርያስ ፡ እምድንበት ፡ ስጠኝ ። ገበቶም ፡ ጂዳለቻ ፡ ጂነጭ ፡ ከርማ ፡ የጂላም ፡ ወተት ፡ አምጣ ፡ ግን ፡ ጥጆች ፡ የደነደኑ ፡ ላምች ፡ የከሱ ፡ ጥጆች ፡ ከስተው ፡ ላሞች ፡ የደነደኑ ፡ እንደሆነ ፡ ወተቱ ፡ ክፉ ፡ ቢሆን ፡ ነው ። ሰውም ፡ ቢጠጣው ፡ በሽተኛ ፡ ይሆናል ፡ አለና ፡ ነገረው ። ጂከርማ ፡ የጂላም ፡ ወተት ፡ አመጣና ፡ እንዴት ፡ ታረጋለህ ፡ አለው ። እሱም ፡ ሲመልስለት ፡ ወግልያ ፡[3] የሚና ፡ ፉጨት ፡ የሚሏቸው ፡ አጋንንት ፡ አሉ ። ለወንዶቹ ፡ ልጆች ፡ አቆራኝለሃለሁ ፡ ኃያል ፡ ይሆናል ፡ ጦርም ፡ አይደፍራቸውም ። ለሴቶቹም ፡ እቴቴ ፡ ጊንቢ ፡ እቴቴ ፡ ሀራ ፡ እቴቴ ፡ ዱላ ፡ የሚሏቸው ፡ አጋንንት ፡ አቆራኝለሃለሁ ። በጂከርማ ፡ ደም ፡ አጠጣቸው ፡ የጂቱን ፡ ላም ፡ ወተት ፡ በዳወሮና ፡ በከተታ ፡

(1) *C*, p. 111-112 : ባፄ ፡ መላክ ፡ ሰገድ ፡ ጊዜ ፡ አዝማች ፡ እንድርያስ ፡ የሚሉት ፡ መኮንን ፡ የደዋሮ ፡ የፈጠጋር ፡ ጌታ ፡ ነበረ ። ዱሮ ፡ ደጅ ፡ አዝማች ፡ ሲሉ ፡ አዝማች ፡ ይሉ ፡ ነበር ። አዝማች ፡ እንድርያስ ፡ ዘመቻ ፡ ዘመተና ፡ በጥቂር ፡ ምድር ፡ ላሉን ፡ ማረከና ፡ አመጣው ፡ ከዚህ ፡ አሳደገና ፡ ላም ፡ ራስ ፡ አደረገው ። የጌታውን ፡ ከብት ፡ ይዘ ፡ ይኖር ፡ ነበር ። ዱሮ ፡ ባርያ ፡ የሚባል ፡ የተማርከ ፡ ነበር ። ላሉም ፡ ባርያ ፡ ነው ። ረኃብ ፡ ዘመን ፡ ሆነ ። ያዜ ፡ መላክ ፡ ሰገድ ፡ የትልድ ፡ ወይዘሮ ፡ ነበረች ። ረኃብ ፡ ቢጸናባት ፡ ወተት ፡ ቢያጠጣኝ ፡ ብላ ፡ አላሉ ፡ ዘንድ ፡ ሄደች ፡ የቅቤ ፡ ንፍሮ ፡ አበላች ።

(2) *C* : እነዚህን ፡ ወለደች ። ፬ቱ ፡ ወንዶች ፡ የሰው ፡ ከብት ፡ እያረዱ ፡ አስቸገሩ ። ድኃው ፡ ተሰብስበ ፡ ላዝማች ፡ እንድርያስ ፡ ጮኸ ። አዝማች ፡ እንድርያስ ፡ ልጆቹህ ፡ የሰው ፡ ከብት ፡ አረዱ ፡ ብሎ ፡ ላሉን ፡ ተቁጣው ፡ ላሉም ፡ ልጆቹን ፡ ተቁጣ ፡ ልጆቹም ፡ አንተውም ፡ አሉት ፡ ቢቸግረው ፡ ከገበቶ ፡ ዘንድ ፡ ሄደ ። ልጆች ፡ የሰው ፡ ከብት ፡ አረዱ ፡ ብሎ ፡ ጌታዬ ፡ ተቁጣ ፡ እንተንም ፡ እገልሃለሁ ፡ ልጆችህንም ፡ እፈጃቸዋለሁ ፡ አለ ፡ ምን ፡ ያበጅኖል ፡ አለው ።

(3) *C* : ወሚኖ ፡

መካከል ፡ ጋላ ፡ የሚሉት ፡ ወንዝ ፡ አለ ። ወተቱን ፡ ከወሀው ፡ ጨምረው ፡ ከውስጡ ፡ ያሉትን ፡ አጋንንት ፡ አቆራኛቸው ፡ እንግዳ ፡ ቋንቋ ፡ አናገራቸው ።[4] ማሎ ፡ ማሎ ፡ ከቱ ፡ ከቱ ፡ ዳሬ ፡ ዳሬ ፡[4] አሰኛቸው ፡ ዕፀ ፡ ሠጢራ ፡ በወንዙ ፡ ስም ፡ ጋላ ፡ ተባሉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የጌታቸውን ፡ ከብት ፡ ይዘው ፡ ከዱ ። አጋንንት ፡ ክደትን ፡ እብለትን ፡ መቀማትን ፡ መስረቅን ፡ አስተማሯቸው ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ የጋኔን ፡ ሥራ ፡ ነው ።[5] ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ካዝማች ፡ እንድርያስ ፡ ጋራ ፡ ተዋግቶ ፡ ላሙን ፡ ነድቶ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ልጆቹን ፡ ይዘ ፡ ጋላ ፡ ከሚባል ፡ ወንዝ ፡ ገበቶ ፡ ጐጆ ፡ ሠርቶ ፡ ቡን ፡ ጫት ፡ እየበላ ፡ ተቀመጠ ። ያጋኔን ፡ መጥቶ ፡ ለኔ ፡ ስገድ ፡ አለው ፡ ከእንድርያስ ፡ እጅ ፡ አውጥቸሃለሁና ፡ አለው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ላሎ ፡ ሂዶ ፡ ሚስቱን ፡ ነይ ፡ እንስገድ ፡ አላት ። እሷም ፡ እኔ ፡ ያለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አልሰግድም ፡ አላቸው ፡ እኔ ፡ እዱር ፡ ገብቼ ፡ አልሰግድም ፡ የእስራኤል ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ አለችው ። ያን ፡ ጊዜ ፡ላሎ ፡ በብትር ፡ እንስቶ ፡ መታት ፡ ሞተች ፡ ስማዕትነት ፡ ደረሰላት ። ላሎን ፡ ግን ፡ ያው ፡ ጋኔን ፡ እሳት ፡ ጠብሶ ፡ ገደለው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያን ፡ ጋኔን ፡ አምጥቶ ፡ ልጆቹን ፡ እንግዳ ፡ ቋንቋ ፡ አናገራቸው ፡ ለሱም ፡ አሰገዳቸው ። ዳግም ፡ እርስበርሳቸው ፡ አጋባቸው ፡ አያንቱን ፡ ለከረዩ ፡ አልኮን ፡ ለቱላማ ፡ ዱረቲን ፡ ለሜጫ ፡ አጋባና ፡ እኔ ፡ ያባታችሁ ፡ አባት ፡ ገበቶ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ፩ድን ፡ ጋኔን ፡ እያመጣ ፡ ይህ ፡ ፈጣሪያችሁ ፡ ነው ፡ አላቸው ፡ እንድም ፡ አዳም ፡ ነው ፡ ስገዱለት ፡ አላቸው ፡ እንዲህ ፡ ማለቱ ፡ እናታቸው ፡ የማን ፡ ነሽ ፡ ሲሏት ፡ ያዳም ፡ አዳም ፡ የማን ፡ ነው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ትላቸው ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ እያታችሁ ፡ ነኝ ፡ እያለ ፡ በወግልያ ፡ አሳመናቸው ። እንደ ፡ አምላክ ፡ ስገዱለት ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ስገዱ ፡ አላቸው ። እንዲት ፡ ቀን ፡ እነሱም ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፡ እናታችን ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ እትስገዱ ፡ ብላናለች ፡ እንተ ፡ ወደ ፡ ጨለማ ፡ ስገዱ ፡ ለምን ፡ ትለናለህ ፡ አሉት ። ያለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያለመስቀል ፡ ያለታቦት ፡ አልሰግድም ፡ ብትል ፡ እናታችንን ፡ አባታችን ፡ ቢመታት ፡ ሞተች ፡ ማርያም ፡ የሚሏት ፡ ሴት ፡ ወይዘሮ ፡ መጥታ ፡ ወተት ፡ አጠጥታ ፡ ተብሲል ፡ ቅብዕ ፡ አብልታ ፡ ብርሃን ፡ እንደ ፡ ሽማ ፡ ስታለብሳት ፡ አየን ። እኛም ፡ እንደ ፡ እናታችን ፡ እንሆናለን ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ እንሰግድም ፡ አሉት ። አወቁብኝ ፡ አለና ፡ ስማችሁ ፡ አላቸው ፡ እኔም ፡ እንጂ ፡ ማርያም ፡ እመቤቴ ፡ ናት ፡ እሰግድላት ፡ ነበርሁ ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ እናታችሁ ፡ ሞታለች ፡ አላቸው ። እኔ ፡ ከናንት ፡ በፊት ፡ ተወልጃለሁ ፡ የናታችሁን ፡ ግብር ፡ አውቃለሁ ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ እንዲህ ፡ አሉት ። እስኪ ፡ ታወቅህ ፡ የናታችንን ፡ እምልክ ፡ ንገረን ፡ አሉት ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ደነገጠና ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አሰበ ። መስቀልን ፡ የሰኔ ፡ ሚካኤልን ፡ አስተርእዮ ፡ ማርያምን ፡ ከትንሥኤ ፡ ጋራ ፡ አክብሩ ፡ ሲነጋ ፡ ሲነጋ ፡ ወደ ፡ ፀሐይ ፡ መውጫ ፡ ስገዱ ፡ አላቸው ። እንዲህ ፡ ማለቱ ፡ በነዚህ ፡ በዓላት ፡ እናታቸው ፡ ስትመጻውት ፡ ስታከብር ፡ ያውቅ ፡ ነበርና ፡ ከአምልክ ፡ ጣዖት ፡ እንዳይሸሹበት ፡ ነው ።

[4] *C* : ማሎ ፡ ጋላ ፡ ማሎ ፡ ጋላ ።
[5] Ici s'arrête le texte de *C*.

ዳግመኛም ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፡ የናታችን ፡ ሥርዓትና ፡ ትምህርት ፡ አለ ፡ የረርና ፡ አለ ፡ ዝቋላ ፡ እንዳትማሩ ፡ ብላናለች ፡ አሉት ። እንዴት ፡ እንሁን ፡ አገሩን ፡ መንገዱን ፡ አናውቀውም ፡ አሉት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እኔ ፡ አውቀዋለሁ ፡ አለና ፡ ከሀገራቸው ፡ እስከ ፡ እግረ ፡ የረር ፡ አደረሳቸው ። በዝቋላ ፡ መሀከል ፡ አኖራቸውና ፡ ወደ ፡ ነቢ ፡ ከሚባል ፡ በታ ፡ እዛፍ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ አጋንንትን ፡ ጠርቶ ፡ ሰብስቦ ፡ ቅረቡ ፡ የናታችሁን ፡ ሥርዓትና ፡ ትምህርት ፡ የሚያውቁ ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፡ ያስተምሯችሁ ፡ አላቸው ። ከነዚያ ፡ አጋንንት ፡ ፫ወርጎ ፡ ሙሉ ፡ ተማሩ ።[6]

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከረዩ ፡ ቱላማ ፡ ሜጫ ፡ ጋሻ ፡ ጋሻቸውን ፡ ይዘው ፡ ከፊት ፡ ቀደሙ ። ወሎ ፡ ከእጎቶቹ ፡ ጋራ ፡ ከብቶቻቸውን ፡ ይነዳ ፡ ዠመር ። አዋሽ ፡ ሲደርሱ ፡ የሚመራቸው ፡ ሰይጣን ፡ ጂክታብ ፡ ከትበ ፡ አዋሽ ፡ ጣለላቸው ። ፩ን ፡ ወሎ ፡ አነሳው ፡ ፮ቱን ፡ ላሞች ፡ በጎች ፡ ፍያሎች ፡ በሉባቸው ። ወሎ ፡ ይኸንን ፡ አነሣሁ ፡ ብሎ ፡ ቢነግራቸው ፡ የኛን ፡ ፈንታ ፡ ማን ፡ ወሰደው ፡ አለ ። አዋሽ ፡ ከብቶች ፡ በሉት ፡ አላቸው ። አዋሽ ፡ ማለት ፡ ቀበኛ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ በላሞች ፡ ስም ፡ አዋሽ ፡ ተባለለ ። እንዴት ፡ እንሆናለን ፡ ብለው ፡ አነከረዩ ፡ አለቀሱ ፡ ያ ፡ ጋሬን ፡ አይዟችሁ ፡ ላምቹን ፡ በጎቹን ፡ ፍያሎቹን ፡ እረዷቸው ፡ ከሞራቸው ፡ ላይ ፡ መልክት ፡ ታገኛላችሁ ፡ አላቸው ። አረዱና ፡ ከሞራቸው ፡ ላይ ፡ ሐንዱራ ፡ ሐንዱራ ፡ የሚሉ ፡ መልክቶች ፡ አገኙ ። በዚያው ፡ አስተማሯቸው ።

ጌታቸውም ፡ አዝማች ፡ እንድርያስም ፡ ሠራዊት ፡ አስከትተው ፡ ዘመቱባቸው ። እነከረዩም ፡ ያ ፡ የሚመራቸው ፡ ጋሬን ፡ ያስተማራቸውን ፡ ሞራ ፡ አይተው ። ጦር ፡ ሆነው ፡ ተዋጉት ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ገደሉት ። ያ ፡ ገሬን ፡ አቡ ፡[7] ወሰደ ፡ አስቀመጣቸው ።[8]

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሽታ ፡ አደረባቸው ፡ እነሱም ፡ ያን ፡ ጋሬን ፡ መድኃኒት ፡ ስጠን ፡ የማርያም ፡ ስም ፡ ጨምረህ ። እናታችን ፡ ያለማርያም ፡ ስም ፡ መድኃኒት ፡ አይሆንም ፡ ብላናለች ፡ አሉት ። አውንም ፡ ስሟን ፡ ጠርተህ ፡ ስጠን ፡ አሉት ። እኔም ፡ አውቃለሁ ፡ እንዲህ ፡ እንዳላችሁ ፡ ሴቶቻችሁ ፡ ሮብ ፡ ቀን ፡ ተሰብስበው ፡ ትብሲል ፡ ቅብዕ ፡ እድርገው ፡ እቴቴ ፡ ግንቢ ፡ እቴቴ ፡ ሐራ ፡ እቴቴ ፡ ዱላ ፡ እልል ፡ እልል ፡ መረማ ፡ እያሉ ፡ ይዝፈኑ ፡ ነወር ፡ ነወር ፡ እያሉ ፡ ጥንባሆ ፡ እየጠጡ ፡ ተብሲል ፡ ቅብዕን ፡ እየበሉ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ትድናላችሁ ፡ አላቸው ። ተብሲል ፡ ቅብዕ ፡ ማለት ፡ በጋላ ፡ ቅንጨ ፡ ማለት ፡ ነው ። ባማራ ፡ በቅቤ ፡ የተቀቀለ ፡ የገብስ ፡ ክክ ፡ ንፍሮ ፡ ማለት ፡ ነው ። ዕፀ ፡ ሠጠጢራ ፡ ማለት ፡ ጥንባሆ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ጥንባሆ ፡ መጠጣት ፡ የቅቤ ፡ ንፍሮ ፡ መብላት ፡ ትዕቢትና ፡ ዝሙት ፡ አምልክ ፡ ባዕድ ፡ ያመጣልና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

(6) Ici reprend le texte de *C*.

(7) *C* : ውሰድ ፡ አቡ ፡

(8) *C* ajoute ici : ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ስገዱ ፡ አላቸው ፡ እርሳቸው ፡ እርግ ፡ እናታችን ፡ እንዲህ ፡ አትሰግድም ፡ ነበር ፡ አሉት ። እርሱም ፡ በሉ ፡ እንዲህ ፡ ስገዱ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ አስገዳቸው ። ብታቸው ፡ ቢሆኑ ፡ ሴት ፡ ቢያጡ ፡ እቶቸውን ፡ አገቡ ። et omet le paragraphe suivant du texte *B*.

[9] ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከረዩ ፡ አያንቱን ፡ ያገባና ፡ አሩሲን ፡ ይቱን ፡ ጦሙጋን ፡ ሱባን ፡ ድንጉርጉርን ፡ [10] ጂሌን ፡ አራያን ፡ ዓዘቦን ፡ አሼንጌን ፡ ጮፋን ። ደግመኛም ፡ የሱፍ ፡ መሐመድን ፡ ልጅ ፡ አግብቶ ፡ ተጎሪን ፡ ኑርን ፡ ወለደ ። ከንብ ፡ ገደል ፡ አስከ ፡ አምባሰል ፡ ከአዳል ፡ አስከ ፡ ጥልጣል ፡ ከትግሬ ፡ በመለስ ፡ ምሥራቁን ፡ ሁሉ ፡ ይዘውታል ። ምድረ ፡ ወገግን ፡ አስቦትንም ፡ ጨርጨርንም ፡ ይዘውታል ። [11] ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቱለማ ፡ አልከን ፡ አገባና ፡ ሰዶን ፡ ዲሉን ፡ አቢቹን ፡ ግምቢቹን ፡ ወበረን ፡ ገላንን ፡ አዳን ፡ ሉሚን ፡ ዋዩን ፡ ጉለሌን ፡ ማታን ፡ ዱበርን ፡ ዳራን ፡ ቦሮናን ፡ ስላሌን ፡ አቦቱን ፡ ይወልዳል ። ዳግመኛም ፡ ከረዩ ፡ ቢሞት ፡ ቱለማ ፡ ሚስቱን ፡ ወርሰ ፡ አራያ ፡ ያሉትን ፡ ወለደ ። አንድም ፡ ጅሌ ፡ የዛር ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ይላሉ ። አከረዩ ፡ በረት ፡ ወድቆ ፡ ቢገኝ ፡ የበረት ፡ ልጅ ፡ አደረገው ። ዳግመኛም ፡ ያባቱን ፡ ሚስት ፡ ወረሰና ፡ ዳወሮ ፡ ያሉቱን ፡ ጋሎች ፡ ይወልዳል ። እነዚህም ፡ አጨበር ፡ ወረዳወሮ ፡ ይባላሉ ። ሜጫም ፡ ዱረቲን ፡ ያገባና ፡ ኩታዬን ፡ ጅማ ፡ አባጅፋርን ፡ ዋጊቱን ፡ ሲቡን ፡ ጨሊያን ፡ ጉዱሩን ፡ ጉማን ፡ ሊሙን ፡ ሌቃን ፡ ወለጋን ፡ አሞሮን ፡ ሆሮን ፡ ጌራን ፡ ጨቦን ፡ ጊዳን ፡ ጅባትን ፡ ሊሙን ፡ ይወልዳል ። እናርያና ፡ ቁጫን ፡ ከውርሻ ፡ ሚስቱ ፡ ወለዳቸው ። እናታቸው ፡ ጥቁር ፡ ሻንቅላ ፡ አይጥ ፡ የምትበላ ፡ ናት ፡ ይላሉ ።

ወሎ ፡ ግን ፡ ያ ፡ የሚመራቸው ፡ ጋኔን ፡ የሰጠውን ፡ ክታብ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ቃልቾች ፡ ሐረርጌ ፡ ሄደ ፡ አስተምሩኝ ፡ አላቸው ፡ ይህስ ፡ የያዝከው ፡ የጅን ፡ ክታብ ፡ ነውና ፡ የኛን ፡ ተማር ፡ ብለው ፡ የስላም ፡ ክታብ ፡ አስተማሩት ። ግራኝ ፡ ከሐረርጌ ፡ ሲመጣ ፡ ባንድ ፡ መጣ ። ከዋያት ፡ ወድያ ፡ ያሉትን ፡ ክርስቲያን ፡ አጥፍቶ ፡ ሰጠው ፡ የሀገሩ ፡ ስም ፡ ሳክ ፡ መልዛ ፡ ነበር ። በሱ ፡ ስም ፡ ወሎ ፡ ተባለ ። ፯ ሚስቶች ፡ አገብቶ ፡ ከ ፯ ለይ ፡ ቤት ፡ ሠራ ። ከ ፯ ሴቶች ፡ ፯ ልጅ ፡ ወለደ ፡ ታላቁን ፡ ልጅ ፡ ሄበኖ ፡ አለው ፡ ከዚህ ፡ ወድያ ፡ ፯ ቤተ ፡ ወሎ ፡ ተባለ ። ያስተማረው ፡ ቃልቻ ፡ አብሮ ፡ መጠ ፡ መልኩ ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ ነበር ፡ ወረቃሉ ፡ ሲደርስ ፡ በየጁ ፡ ቦታዬ ፡ ይህ ፡ ነወ ፡ ብሎ ፡ አንካሴውን ፡ ተክሎ ፡ ተቀመጠ ። ፴ ሚስት ፡ አገባና ፡ ከ ፴ ው ፡ ሚስት ፡ ፴ ልጅ ፡ ወለደ ። መንደሩ ፡ ቢበዛ ፡ ወረሴክ ፡ ይባላሉ ።

ከረዩ ፡ ቱለማ ፡ ሜጫ ፡ ፪ ነገር ፡ ፩ እናድርግ ፡ ብለው ፡ ተማማሉ ። ፪ ነገር ፡ ማለት ፡ ሴትና ፡ ከብት ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ የጋራ ፡ ቢሆኑ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ሴትና ፡ ከብት ፡ ናቸውና ፡ ሰውን ፡ የሚያጣሉ ፡ አሉ ።

ጋሎች ፡ ባለጌ ፡ መባላቸው ፡ ፩ ሴት ፡ የጋራ ፡ በመያዛቸው ፡ ነው ። ባሮች ፡ መባላቸው ፡ የአባታቸው ፡ የላሎ ፡ ምርከኒት ፡ ነው ። ወተት ፡ ጠጥተው ፡ መኖራቸው ፡ አቢላምነታቸው ፡ ሲመሰክርባቸው ፡ ነው ። ተማርከው ፡ ያለመሸጣቸው ፡ ያንጉሥ ፡ የእጎት ፡ ልጅነታቸው ፡ ነው ።

[9] Le texte de *C* reprend ici.

[10] *C* : ድጉራ ፡

[11] *C*, p. 116, donne ensuite les noms des fils de Mēčča. Époux de Alko, il engendre Soddo Abu, Dulu, Čabu, Gudru, Kwetāy, Omoro, Koru, Lēqā, Çalabā, Wallagā, Gummo, Limmo, Jemmā et Girā. *C* n'indique pas quels furent les descendants de Tulamā.

እንጉሥ ፡ ቤት ፡ ያለማደግደጋቸው ፡ ክንብንብ ፡ ማወቃቸው ፡ የሴት ፡ ወይዘሮ ፡ ልጆች ፡ ንን ፡ ሲሉ ፡ ነው ።

ይህ ፡ የተጻፈው ፡ ዋና ፡ ዋናው ፡ ነው ። በዚህ ፡ የሚበዛ ፡ ንገር ፡ አላቸው ።

(12) ግራኝ ፡ በዛንትራ ፡ በጠር ፡ ሲሞት ፡ ያጼ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ሠራዊት ፡ እንግዲህ ፡ እንተ ፡ ሞትህልን ፡ ጠላት ፡ ጠፉልን ፡ ቢሉት ፡ እኔ ፡ መቸ ፡ ሞትሁ ፡ ቁንጪም ፡ ቁንጪም ፡ ልጆች ፡ ወለኻለሁ ፡ ያለው ፡ (13) ጋሎችን ፡ ነው ። የግራኝ ፡ ዘር ፡ የተከለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይንቀለው ፡ አሜን ።

እነዚህም ፡ እስከ ፡ አጼ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ድረስ ፡ ፷፯ ቤት ፡ ሆነው ፡ በኢትዮጵያ ፡ መልተው ፡ ከክርስቲያን ፡ እኩል ፡ በኩል ፡ ሆነው ። ጥሩ ፡ ክርስቲያንም ፡ እንደነሱ ፡ ግምባራቸውን ፡ ደም ፡ እየተቀቡ ፡ ጥንባሆ ፡ እየጠጡ ፡ በትርሲቲ ፡ ኩርቢት ፡ እየዘፈኑ ፡ ጋሎችን ፡ እያዩ ፡ እምልከ ፡ ባዕድ ፡ ሠሩ ። አጼ ፡ ልብነ ፡ ድንግልም ፡ የመስቀል ፡ ዕለት ፡ ፈረሳቸውን ፡ ደም ፡ ቀብተው ፡ እሳቸውም ፡ ደም ፡ ግምባራቸውን ፡ ተቀብተው ፡ ጥምባሆ ፡ ጠጥተው ፡ ፈረስ ፡ ጨወታ ፡ ወጡ ። ሠራዊቱም ፡ ከማን ፡ ጋራ ፡ እንዋጋ ፡ በከን ፡ [አሏቸው ።] ያን ፡ ጊዜም ፡ ተነገሡ ፡ ፲፱ ፡ ዓመት ፡ ነበር ። መዋጋት ፡ እንዳንረሳ ፡ እርስበርሳችን ፡ እንዋጋ ፡ አሉ ። ሲዋጉም ፡ የንጉሥን ፡ ግምብ ፡ አፍርሰው ፡ ዋሉ ። ንጉሡም ፡ በጨዋታ ፡ ግምቡ ፡ ቢፈረስ ፤ ከታች ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወጥተው ፡ መናገሻ ፡ አፋፍ ፡ ተቀመጡ ፡ እዚያ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ሠራዊቱን ፡ ቢያዩ ፡ በባር ፡ ሜዳ ፡ በከሰ ፡ ሜዳ ፡ መልቶ ፡ እዩት ። ዳግምኛም ፡ ፴ ዓመት ፡ የሆነው ፡ ፴ ዓመት ፡ የሆነው ፡ ጐልማሳ ፡ ይቁጠር ፡ ብለው ፡ አዘዙ ። ቢቆጠር ፡ ፯፻፲ ሆነ ፡ የሠራዊታቸውን ፡ ብዛት ፡ አይተው ፡ ትዕቢት ፡ ኩራት ፡ አድሮባቸው ፡ ነበርና ፡ እንዲህ ፡ አሉ ። ፈርዖንና ፡ ስናክሬም ፡ አንጥያክስና ፡ ናቡከደነጾር ፡ እነዚህ ፡ ፬ ቱ ፡ ነገሥታት ፡ በጠርነት ፡ ቢገጥሙኝ ፡ አይቆሙልኝም ፡ ነበር ። እባክህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጦር ፡ አምጣልኝ ፡ አሉ ፡ ሠራዊቱም ፡ እርስበርሳችን ፡ ሆነን ፡ ከመዋጋት ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንለምን ፡ አሉ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ጫን ፡ ዕጣን ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖስ ፤ ጫን ፡ ዕጣን ፡ ለጣና ፡ ቂርቆስ ፡ ላኩ ። ይህን ፡ እያጠናችሁ ፡ ስብሐት ፡ ፍቁር ፡ እያደረሳችሁ ፡ ጦር ፡ አምጣለት ፡ እያላችሁ ፡ እዘኑልኝ ፡ ብለው ፡ ላኩ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ቄስ ፡ አጼ ፡ ዮሐንስ ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ቃለ ፡ እዋዲ ፡ እራቅ ፡ ማሰሪ ፡ ዘመለከት ፡ የንጉሡ ፡ ወዳጆች ፡ ነበሩ ። ይኸንን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ መነከሳት ፡ እንምከራቸው ፡ ብለው ፡ ገቡ ። ገብተውም ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ እንድ ፡ ጊዜ ፡ ይስሙን ፡ ቁርጥ ፡ ወዳጆችም ፡ ነንና ፡ አሏቸው ። ንጉሡም ፡ እሺ ፡ አሉ ። ከእግዚአብሔር ፡ የሚያጣልምን ፡ ንገር ፡ ለምን ፡ ይሠራሉ ። ንጉሥ ፡ ሆነው ፡ ከሠራዊትዎ ፡ ጋር ፡ በጨዋታ ፡ ለምን ፡ ግምብዎን ፡ ያፈርሳሉ ። ደግሞስ ፡ ንዳያን ፡ ምጽዋት ፡ ፈልገው ፡ ቢመጡ ፡ ለምን ፡ በፈረስ ፡ እግር ፡ ፈጭዋ

(12) *C*, p. 118, ajoute : ግራኝ ፡ በዘንትራ ፡ ደገች ፡ በጸር ፡ ሲሞት ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፡ ኢድሜዬ ፡ ፴ ነበረ ፡ እኔ ፡ ከፉት ፡ አበዛውና ፡ ፳ ቀደ ፡ ቁንጮ ፡ ፲፭ ዓመት ፡ አደረገችብኝ ፡ አለ ።

(13) *C*, p. 119, ajoute : ዓዕረ ፡ ሞት ፡ ይዘት ፡ ሳለ ።

ቸው ። ከዚህ ፡ ቀደሞ ፡ አያትዎ ፡ አፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ መልካሞ ፡ ንጉሥ ፡ ነበሩ ። ደግ ፡ ሲሠሩ ፡ ቢያይ ፡ ሰይጣን ፡ ቀንቶ ፡ የመስቀል ፡ ዕለት ፡ በፈረስ ፡ ሲጫወቱ ፡ በፈረበ ፡ እግር ፡ ብዙ ፡ ነዳያን ፡ አለቁ ። በዚሁ ፡ ነገር ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሐዋርያት ፡ ንጉሡን ፡ ቢሰድቧቸው ፡ ንጉሡም ፡ ሊቃውንቱን ፡ ሰብስበው ፡ ንጉሥ ፡ ሆኝ ፡ ሰድበኛልና ፡ መጽሐፍ ፡ አይታችሁ ፡ ሽሩልኝ ፡ አሉ ። ሊቃውንቱም ፡ ተሰብስበው ፡ ንጉሥ ፡ በክርስቶስ ፡ ዘንድ ፡ ጻድቅ ፡ ወመሢሕ ፡ ከማየ ፡ የተባለው ፡ በመልአክ ፡ እጅ ፡ የተቀባውን ፡ በሃይማኖት ፡ ነገር ፡ ተሰደበ ፡ ወንጌል ፡ ሲል ፡ ኩሉ ፡ ኃጢአት ፡ ወጽርፈት ፡ ይትኃደግ ፡ ወዘጸረፈ ፡ ላዕለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኢይትኃደግ ፡ ኃጢአቱ ፡ ብሏልና ፡ ይቀጣ ፡ ብለው ፡ ፈረዱባቸው ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ ፮ ባሮች ፡ ልከው ፡ እዱር ፡ ውስጥ ፡ አግብተው ፡ ፮ ባሮች ፡ እየተፈራረቁ ፡ ፀሐይ ፡ ወጥቶ ፡ እስኪገባ ፡ ድረስ ፡ ገረፏቸው ። ያን ፡ ጊዜ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሐዋርያት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በካህናቱም ፡ በንጉሡም ፡ አዘኑ ። ከዚያ ፡ ወድያ ፡ እመቤታችን ፡ መጥታ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሐዋርያትም ፡ አጼ ፡ ዘርአ ፡ ያዕቆብንም ፡ ትወዳለችና ፡ በራዕይ ፡ መጥታ ፡ ተክለ ፡ ሐዋርያት ፡ በመገረፍህ ፡ አትዘን ፡ ቀድሞ ፡ ስማዕትነትን ፡ አሰኝኝ ፡ ትለኝ ፡ ነበር ። እሁንም ፡ ከልጄ ፡ ለምጄልሃለሁ ፡ አንተም ፡ ዘርአ ፡ ያዕቆብ ፡ ቀድሞ ፡ ልጄ ፡ የአብ ፡ ልጅ ፡ ነበር ፡ ለአድኅኖ ፡ ዓለም ፡ ብሎ ፡ ከኔ ፡ ቢወለድ ፡ አይሁድ ፡ ወልደ ፡ ዮሴፍ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ብለው ፡ ሰደቡት ። እኔስ ፡ ዘርአ ፡ ዳዊት ፡ ንጉሥ ፡ አልነበርኩምን ፡ ብሎ ፡ አብ ፡ የባሕርይ ፡ አባቱን ፡ ማርልኝ ፡ ብሎ ፡ ለመነ ፡ እንጂ ፡ ላጥፋቸው ፡ አላለም ። እሁንም ፡ ታረቁ ፡ ብላ ፡ አስታረቀቻቸው ። አጼ ፡ ዘርአ ፡ ያዕቆብም ፡ ከጦር ፡ ጊዜ ፡ በተቀር ፡ ፈረስ ፡ ጨዋታ ፡ ውጊያ ፡ ይቅር ፡ አሉ ። እስዎስ ፡ ጥንቱን ፡ በፈረስ ፡ መጫወትዎ ፡ ለፍቅር ፡ ለአክብሮ ፡ በዓለ ፡ መስቀል ፡ አልነበረም ። ዳግመኛስ ፡ ጦር ፡ አምጣልኝ ፡ ብለው ፡ ዕጣን ፡ ማሳጠንዎ ፡ ቢቸግርዎ ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ ቀጥ ፡ አድርጎ ፡ ከምድር ፡ ዳር ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ዳር ፡ ድረስ ፡ ቢያስገዛዎ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ አላማረም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ያመግልና ፡ ንስሐ ፡ ይግቡ ፡ በነዚህ ፡ ነዳያን ፡ ሞት ፡ ቸር ፡ ነው ፡ መሓሪም ፡ ከግፍዓ ፡ ነዳያን ፡ ግን ፡ መስተበቅል ፡ ነውና ፡ አይሆንም ፡ አሏቸው ።

ይኸን ፡ ነገር ፡ ቢመክሩቸው ፡ ትዕቢት ፡ አድሮባቸው ፡ ነበርና ፡ ገፋዔ ፡ ነዳያን ፡ አደረጋችሁኝ ፡ ብለው ፡ ተቆጥው ፡ ከድንኳን ፡ ገብተው ፡ ግብር ፡ አላገባም ፡ ብለው ፡ ከሰው ፡ ሳይገናኙ ፡ ፫ ቀን ፡ አደሩ ።

ያን ፡ ጊዜ ፡ ሮማውያን ፡ ግብጻውያን ፡ ከጽርዕ ፡ መነኩሴ ፡ ጋር ፡ መጽሐፈ ፡ መነከሳትን ፡ ለማስተማር ፡ መጥተው ፡ ነበር ። እጨጌ ፡ ዕንባቆም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ አዘኑ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ እጨጌ ፡ ቢያዘኑ ፡ ሮማውያን ፡ ካዔ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘንድ ፡ ገብተው ፡ እንዲህ ፡ አሉ ። ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ቢመክሩህ ፡ ለምን ፡ ትቆጣለህ ። እሁንም ፡ ከነዚህ ፡ መነከሳት ፡ ጋራ ፡ መጽሐፍ ፡ በተናገረው ፡ ቃል ፡ ታረቅልን ፡ አሏቸው ። ይህን ፡ ነገር ፡ ሰምተው ፡ ዝም ፡ አሉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የንጉሥ ፡ ቢትወደድ ፡ ዘሚካሌል ፡ የሚባል ፡ ጠንቋይ ፡ ነበር ። ቂስ ፡ አፄ ፡ ዮሐንስን ፡

አይወደውም ፡ ነበር ፡ ሃይማኖቱ ፡ ልዩ ፡ ነበርና ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ ንጉሥን ፡ እነዚህ ፡ ሮማውያን ፡ የርስዎ ፡ ወዳጆችዎ ፡ ናቸው ፡ ብዙ ፡ መጽሐፍ ፡ ያውቃሉ ፡ ቄስ ፡ አፄ ፡ ዮሐንስ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ እርስዎንም ፡ ጳጳሱንም ፡ ያማል ፡ ዛሬ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ከሮማውያን ፡ ጋራ ፡ አይጣሉ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ያካ[ሰ]ሱን ፡ ረትቼ ፡ ላብርልዎ ፡ አላቸው ። ይሁን ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ነው ፡ አሉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሮማውያንን ፡ እማኝ ፡ አድርገው ፡ አስከሰሷቸው ። ዘሚካኤል ፡ ከሰ ፡ ቆመ ፡ ጥንባሆ ፡ መጠጣት ፡ ሰውን ፡ ያረክስዋልን ፡ ይህ ፡ ንጉሥ ፡ ጥንባሆ ፡ ሲጠጣ ፡ ጳጳሱ ፡ ምነው ፡ አይመክር ፡ ብላችሁ ፡ ንጉሡንም ፡ ጳጳሱንም ፡ አማችሁ ፡ አላቸው ። እነዚያም ፡ አምን ፡ በአፄ ፡ ዘርአ ፡ ያዕቆብ ፡ በናዖድ ፡ ዘመን ፡ ከህናቱም ፡ መኳንንቱም ፡ ጻድቃን ፡ ነበሩ ። በሃይማኖት ፡ ጽድቃቸውም ፡ የታወቀ ፡ ነበረ ፡ በክርስቶስ ፡ ዘንድ ፡ በሥርዓተ ፡ ሐዋርያት ፡ ቃል ፡ ወንጌልን ፡ ያስተማሩ ፡ ነበሩ ። ዛሬ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ንጉሥ ፡ ያባቱን ፡ ትምህርትና ፡ ግዝት ፡ አፍርሰ ፡ ቃላቸውን ፡ ቢንቀው ፡ እንግዲያው ፡ ቃለ ፡ መጽሐፍ ፡ መፍረሱ ፡ ነው ፡ ብለናል ። ጳጳሱንም ፡ ለምን ፡ ሮማውይን ፡ ፪ ባሕርይ ፡ እያሉ ፡ ያስተምራሉ ፡ ሃይማኖቱ ፡ እስክንድርያ ፡ መጥፋቷ ፡ አይደለም ፡ ብለናል ። ይህ ፡ ሐሜት ፡ አይሆንብንም ። የጻድቃን ፡ ቃላቸው ፡ ከፈረሰ ፡ ጌታም ፡ ባ ፬ ወንጌል ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ፡ ዘተወክፈ ፡ ጻድቅ ፡ አሰበ ፡ ጻድቅ ፡ ወዕሜቱ ፡ ጻድቅ ፡ ይነሥእ ፡ እምጎበ ፡ እግዚአብሔር ። ወዘኪያክሙ ፡ አበየ ፡ ኪያየ ፡ አበየ ፡ ወዘኪያክሙ ፡ ሰምዓ ፡ ኪያየ ፡ ሰምዓ ። ለእለ ፡ ኃደግሙ ፡ ኃጢአት ፡ ይትኃደግ ፡ ለሰብእ ፡ ወለእመ ፡ ኢኃደግሙ ፡ ኢይትኃደግ ፡ ሎሙ ። ወዘአሰርክሙ ፡ በምድር ፡ ይኩን ፡ እሡር ፡ በሰማያት ፡ ብሏልና ፡ ቃላቸውን ፡ ገድላቸውን ፡ ተነቀፈ ፡ ቃለ ፡ ወንጌል ፡ መፍረሱ ፡ ነው ፡ ብለናል ፡ አሉት ። እሱም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መለሰላቸው ። እንግድያውስ ፡ በወንጌል ፡ ታመናችሁ ፡ ኢያረኩስ ፡ ለሰብእ ፡ እንተ ፡ በአ ፡ ውስተ ፡ አፉሁ ፡ ይላል ፡ ለምን ፡ ጥንባሆ ፡ ብንጠጣ ፡ ትረክሳላችሁ ፡ ትሉናላችሁ ፡ አሏቸው ። እነሱም ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፡ አንተስ ፡ ኢያረኩሰን ፡ ትመለከታለህ ፡ አላ ፡ ዘይወጽእ ፡ እምልቡናሁ ፡ አምልክ ፡ ባዕድ ፡ ገቢረ ፡ ሥራይ ፡ ማለቱን ፡ አታየውምን ፡ አሉት ። እንተ ፡ ግን ፡ አሁን ፡ እንዲህ ፡ ማለትህ ፡ ሰብአ ፡ ግብጽና ፡ ሰብአ ፡ ሮም ፡ በሀገራቸው ፡ አምልክ ፡ ባዕድ ፡ ቀርቷል ። በወንጌል ፡ አምነዋል ፡ በልማደ ፡ ሀገር ፡ ጥንባሆ ፡ ይጠጣሉና ፡ ይረዱኛል ፡ በንገር ፡ ብለህ ፡ ነው ። እኛስ ፡ ጥንባሆ ፡ በመጠጣት ፡ አምልክ ፡ ባዕድ ፡ ሲጠሩ ፡ ቢያይ ፡ አባቶቻችን ፡ ረግመው ፡ ገዝተዋል ። ሐሰት ፡ ነው ፡ ብትል ፡ ገድላቸው ፡ ጠማራቸው ፡ ይመስክር ፡ አሉት ።

ያን ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ተችሎት ፡ ተነሥተው ፡ ሄዱ ፡ ሮማውያን ፡ በፍርድ ፡ አይደሉምና ፡ ያስረቱኛል ፡ ብለው ፡ ከጳጳሱ ፡ ገብተው ፡ አቡን ፡ ስምዖንን ፡ ጠየቋቸው ፡ እውነት ፡ ጥምባሆ ፡ መጽሐፍ ፡ ይከለክለዋል ፡ አሏቸው ። አቡን ፡ ስምዖንም ፡ እንዲህ ፡ አሉ ። እኔ ፡ በሀገሬ ፡ ነውር ፡ ሆኖ ፡ አላገኘሁትም ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ከኔ ፡ ቀድመው ፡ የነበሩ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ሚካኤል ፡ አባ ፡ ማርቆስ ፡ በአያትህ ፡ ዘመን ፡ ከእግዚአችን ፡ ማርያም ፡

ዘንድ ፡ በጠማር ፡ አገኘነው ፡ ብለው ፡ አኩረወት ፡ አገኘሁት ። ከመጽሐፈ ፡ ቅዳሴ ፡ ጋራ ፡ ጽፈወት ፡ በዓረቢ ፡ ቋንቋ ፡ አሏቸው ። ይኸን ፡ ከጳጳሱ ፡ አፍ ፡ ሰምተው ፡ ትዕቢትና ፡ ኩራት ፡ አደሮባቸው ፡ ነበርና ፡ በሮም ፡ በግብጽ ፡ ጥንባሆ ፡ ሲጠጣ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አትጠጡ ፡ የሚል ፡ ቄስ ፡ አይሆንም ፡ እቀጻዋለሁ ፡ ብለው ፡ አዋጅ ፡ ነገሩ ። ይኸን ፡ ስምተው ፡ ካህናቱ ፡ ሁሉ ፡ ይጠጡ ፡ ጀመረ ። እንደ ፡ ጋላም ፡ እየተቀቡ ፡ ለፈረሳቸው ፡ ሜጢቻ ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ።

ፎ ቀን ፡ የደብረ ፡ ምጥማቅ ፡ ቄስ ፡ ሱረት ፡ ጠጥቶ ፡ በነስሩ ፡ በኩል ፡ እሆዱ ፡ ገብቶ ፡ ቅዳሴ ፡ ገባ ። በዚህ ፡ ነገር ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ቢያዝኑ ፡ እመቤታችን ፡ ልትፈቅዳቸው ፡ መጣች ፡ እመቤቴ ፡ አይው ፡ የልጅሽን ፡ ሥጋና ፡ ደም ፡ ከጥንባሆ ፡ ጋራ ፡ ሲበላው ፡ ቄሱ ፡ አሏት ፡ ለምን ፡ ሐዋርያት ፡ በሲኖዶስ ፡ ለጣዖት ፡ ለአምልክ ፡ ባዕድ ፡ የሚታረደውን ፡ በግና ፡ ፍያል ፡ አትብሉ ፡ አሉን ፡ ፍያሉም ፡ ፍያል ፡ በጉም ፡ በግ ፡ አይደለም ፡ ዘወትር ፡ የምንበላው ፡ አሉ ። እንግዲህስ ፡ እመቤታችን ፡ ለዚህ ፡ ቄስ ፡ ብትለመኝው ፡ አማላጅ ፡ ብትሆኝው ፡ አባቶቻችን ፡ ሃይማኖት ፡ የላቸውም ፡ እንቺም ፡ አምላክ ፡ አልወለድሽም ፡ ሁሉም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ የቀድሞው ፡ መጽሐፍ ፤ ካባቶቻችን ፡ ያገኘነው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ። ይኸን ፡ ቢሏት ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ መሥዋዕቱን ፡ ሳይቀበል ፡ ቄሱ ፡ ሞተ ፡ በመቅሠፍት ።

በአጼ ፡ ልብነ ፡ ድንግልም ፡ ዘመን ፡ ግራኝ ፡ የሚሉት ፡ ተነሣ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ ሁሉ ፡ አቃጠላቸው ። ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ሀገራቸውን ፡ ለጋሎች ፡ ትተው ፡ ተሰደዱ ፡ ወደ ፡ ትግሬ ። የግራኝም ፡ አመጣጥ ፡ ፎ መነኩሴ ፡ በሕልሙ ፡ አይቶ ፡ ነገራቸው ። ሕልመም ፡ እንዲህ ፡ ነው ። ፪፪ የጋላ ፡ ዘመን ፡ ፻፳፫ ዘመን ፡ የእስላም ፡ ቢላቸው ፡ ነጉሡም ፡ ደስ ፡ አላቸው ። ከአሕዛብ ፡ ወገን ፡ ዳግም ፡ እነግሣለሁ ፡ ብለው ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

ነጽሐፍ ፡ ነገረ ፡ ግራኝ ፡ ወፍጻሜ ፡ ሞቱ ።

የግራኝ ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ ነው ። በግራኝ ፡ ዘመን ፡ የሞቱትም ፡ የተሰደዱትም ፡ ሰማዕት ፡ የደረሳቸው ፡ ፭፻፺ ሺህ ፡ ፭፻፭፭ ናቸው ። ዜናቸውንም ፡ እንጽፋለን ፡ የሰማው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በሃይማኖት ፡ እንዲጸና ። የግራኝም ፡ የልደቱ ፡ መክንያት ፡ እንዲህ ፡ ነው ። አሕመድ ፡ የሚሉት ፡ እስላም ፡ ያረርጌና ፡ የአዳል ፡ ገጋ ፡ ነበር ፡ ፯፻ነጭ ፡ በቅሎ ፡ ፱ወርቅ ፡ ቡችላ ፡ ፴ከዜ ፡ ምንጠፍ ፡ ሺህ ፡ ምንጠፍ ፡ ሺህ ፡ ፫፻ ሸማ ፡ ፪ ሺህ ፡ ፍሪዳ ፡ ፫ሺህ ፡ የበግና ፡ የፍየል ፡ ሙክት ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ለአጼ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ይገብር ፡ ነበር ። የግራኝ ፡ እናት ፡ የድኃ ፡ ልጅ ፡ ነበረች ፡ ሐፃንነት ፡ ነበራት ፡ መልከ ፡ ነበረች ፡ ስሟም ፡ ሽምሽምያ ፡ ተባል ፡ ነበረ ። ለሽክም ፡

ታዘ ፡ አጼ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ከተማ ፡ ብር ፡ ይዛ ፡ መጣች ። ንጉሡም ፡ ለአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ማሠሪ ፡ ተገንዘባቸው ፡ ሁሉ ፡ ሲሰ ፡ ይሰጡ ፡ ነበር ። ያጼ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ አሽክር ፡ ራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ የሚባል ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያሠራ ፡ ነበር ። የግራኝ ፡ እናት ፡ ከብዙ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ያመጣችውን ፡ ግብር ፡ ተሸክማ ፡ ወረደች ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ከባልንጀሮቿ ፡ ተለይታ ፡ ታማ ፡ ቀረች ። ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ አባላገር ፡ ቤት ፡ ተመራች ። በጐ ፡ ስትሆን ፡ እዚያው ፡ ሀገር ፡ ውሽማ ፡ ያዘችና ፡ ተጠልተው ፡ ተዋጉባት ፡ የሀገሩም ፡ ሰዎች ፡ ቀለብ ፡ ከለከሏት ። ከሹሞች ፡ ዘንድ ፡ ሄዳ ፡ ብትጮህ ፡ ወግጂ ፡ አዋጋሽን ፡ አሏት ፡ የሀገሩም ፡ ስም ፡ አዋጋሽን ፡ ተባለ ። ከዚያ ፡ ተነሥታ ፡ ሴት ፡ ደብር ፡ ተቀመጠች ። ከዚያም ፡ ዳግም ፡ የመነኩሴ ፡ ውሽማ ፡ ያዘች ። ከሷ ፡ ጋር ፡ አድሮ ፡ ህባኔው ፡ መስሎት ፡ ጉፍታዋን ፡ እራሱ ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሄዶ ፡ ደብድበው ፡ ገደሉት ፡ እሷም ፡ አገሩን ፡ አዳል ፡ ሄደች ። ከዚያ ፡ ከመነኩሴ ፡ አርግዛ ፡ ግራኝም ፡ አዳል ፡ ላይ ፡ ተወለደ ፡ እሷም ፡ አገሩን ፡ ለሚገዛ ፡ አሕመድ ፡ ለሚባል ፡ ሰው ፡ አባት ፡ የሌለው ፡ ልጅ ፡ ነውና ፡ አባት ፡ ሁነው ፡ ብላ ፡ ሰጠችው ። እሱም ፡ አሰደገውና ፡ ሽማ ፡ ሥራ ፡ ተማረና ፡ ይሠራ ፡ ዠመር ። ከልጆቹ ፡ ጋራ ፡ ቢጠላ ፡ ይህ ፡ እንድ ፡ ጐድን [14] ፡ ብለው ፡ ሰደቡት ። እንድ ፡ ጐድን ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሽማግሌ ፡ ጠየቀ ። አባት ፡ የሌለው ፡ ማለት ፡ ነው ፡ አሉት ። ሄደና ፡ እናቱን ፡ አባቴን ፡ ንገሪኝ ፡ አላት ። እሷም ፡ አባትህስ ፡ ቄስ ፡ ነበር ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ካህናቶች ፡ ደብድበው ፡ ገደሉት ፡ እንጂ ፡ አሁንም ፡ ወንድ ፡ መሆን ፡ የአባቱን ፡ ደም ፡ መመላስ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አለችው ። ፩ ቀንድ ፡ የሌለው ፡ በሬ ፡ ነበረው ፡ እሱን ፡ አረደና ፡ ተጐበዘች ፡ ጋራ ፡ እዱር ፡ በላና ፡ የሰው ፡ ከብት ፡ እያረደ ፡ ይበላ ፡ ዠመር ። የበሬ ፡ ስም ፡ ጎዴ ፡ ይባል ፡ ነበር [15] ፡ አሁንም ፡ የሀገራችን ፡ ሰዎች ፡ ጎዴ ፡ እንግባ ፡ ይላሉ ፡ የግራኝ ፡ ትምሕርት ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ የሰው ፡ ከብት ፡ አትረድ ፡ ብሎ ፡ አሕመድ ፡ ተቆጣው ። ወዲያው ፡ ግራኝን ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ ሾመው ።

የመነሣቱም ፡ ምክንያት ፡ እንዲህ ፡ ነው ። አጼ ፡ ልብነ ፡ ድንገል ፡ በነገሡ ፡ በ ፲፱ ዓመት ፡ ነው ፡ አሕመድ ፡ ሲሞት ፡ እግዚአብሔር ፡ ገለጠ ለትና ፡ ለግራኝ ፡ ነገረው ፡ ለዚህ ፡ ንጉሥ ፡ አትገዛ ፡ ቢመጣብህም ፡ ድል ፡ ታደርገዋለህ ፡ ልጁን ፡ ኑርን ፡ ሞግዚት ፡ ሆነህ ፡ አሳድገው ፡ ሌላ ፡ ልጅ ፡ የለውምና ፡ ብሎት ፡ ሞተ ። ግራኝም ፡ አሕመድ ፡ ሞተ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ አጼ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ላከ ፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ እሳቸውም ፡ ዓመት ፡ ሰጥቼሃለሁ ፡ ግብሩን ፡ እምጣ ፡ ብለው ፡ ላኩበት ፡ እሱም ፡ አልገብርም ፡ አለና ፤ ላከ ። ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ዲገል [16] ፡ የሚባሉ ፡ እንደራሴያቸው ፡ ነበራቸው ፡ ንጉሡም ፡ ጭፍራ ፡ ቆጥረው ፡ ሰደዱት ፡ እሱም ፡ ዘምቶ ፡ አዳል ፡ ደረሰና ፡ ሰውን ፡ ፈጅና ፡ ከብቱን ፡ ማረከና ፡ ተመለሰ ። ግራኝ ፡

[14] *C* : ፩ ጐን ፡
[15] *C* : የዛሬ ፡ ልጅ ፡ በጸም ፡ እያረጉ ፡ ጎዶ ፡ የሚሉት ፡ የግራኝ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።
[16] *C* : ብላቴንጌታ ፡ ዲጋል ።

ተኋላ ፡ ተከተለና ፡ ሰውነ ፡ ፈጅቶ ፡ ምርከውነ ፡ መለሰና ፡ ወረደ ። ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ በ ፱ ዓመቱ ፡ መጠና ፡ ከነጉሥ ፡ ሠራዊት ፡ ጋራ ፡ ተዋጋ ፡ አጋፋሪያቸው ፡ ቱሉ ፡ ይባል ፡ ሽሽቶ ፡ ቢመጣ ፡ ቱሉም ፡ ፈራ ፡ አሉ ፡ የሀገሩም ፡ ስም ፡ ቱሉፈራ ፡ ተባለ ። ከነጉሡ ፡ ጋራ ፡ በሰመርማር ፡ ተዋጉ ፡ አስከ ፡ ሽነብረ ፡ ከራ ፡ ድረስ ፡ . . . [17]

[17] *C* donne au lieu de ce paragraphe un bref récit des causes du soulèvement de Grāñ, attribué à l'orgueil de Lebna Dengel, voyant la puissance de son armée et désireux de la voir au combat contre un ennemi réel qu'il appelle de ses vœux.

TRADUCTION

Au nom du Père, du Fils et du Saint Esprit, un seul Dieu. Nous écrivons l'histoire des Gallas et de la vision que notre roi Lebna Dengel eut au sujet de son pays. Nous l'avons écrite afin que nos enfants enseignent à la génération future, plus tard, à ne pas renier sa foi lorsqu'elle tombera au pouvoir des païens. Que la prière puissante de la Mère de lumière garde le serviteur de Dieu Takla Wald, aux siècles des siècles, amen [1].

(*a*) Au temps d'*Aṣē* Amda Ṣeyon, sévit une famine cruelle. L'*eṭ̌agē* Fileppos avait maudit notre pays pour une affaire de religion [2] et la misère s'abattit sur lui. Une sœur du roi vivait alors dans l'indigence au Faṭagār. Un certain *azmāč* Endreyās, qui était en ce temps gouverneur du Dāwaro et du Katatā [3] partit en expédition

(*a*) *C :* Au temps d'*Aṣē* Malak Sagad (Sarṣa Dengel) un gouverneur appelé *azmāč* Endreyās était chef du Dawāro et du Faṭagar. On disait jadis *azmāč* pour *dağāzmāč*. L'*azmāč* Endreyās fit une expédition et ramena un captif (nommé) Lālu. Il l'éleva et en fit le pasteur de (son) troupeau. Il gardait le bétail de son maître. Jadis, ce qu'on appelait esclave était un prisonnier de guerre. Lālu était donc esclave. Vint un temps de famine. Il y avait alors une nièce d'*Aṣē* Malak Sagad qui, souffrant de la faim, alla trouver Lālu se disant qu'il lui donnerait du lait. Il lui fit manger de la polenta au beurre.

[1] Cette introduction geez vaut pour l'histoire des Gallas et de Grāñ et pour le *dersāna Rāgu'ēl* qui, dans le manuscrit *B* suit immédiatement le récit des premières défaites de Lebna Dengel.

[2] Le conflit qui opposa l'*eṭ̌agē* Fileppos à Amda Ṣeyon aurait eu pour cause le mariage du roi avec une veuve de son père : voir le *Gadla Fileppos* (de Dabra Libānos) édité par B. Turaiev (*Corpus scriptorum christianorum orientalium,* Aethiop. series altera, t. XX, traduction, p. 209 et suiv.). Selon le *Gadla Anorēwos* (trad. Conti Rossini, *CSCO,* XX, p. 83), l'initiative de la protestation aurait été prise par *abbā* Anorēwos, même version dans les *chroniques* abrégées (voir R. Basset, *Journal Asiatique,* août-septembre 1881, p. 94 et F. Beguinot, *La cronaca abbreviata,* Rome, 1901, p. 10); une chronique abrégée manuscrite en ma possession donne une autre version de l'origine du conflit : le roi aurait commis l'inceste avec sa sœur. Les actes de Baṣalota Mikā'ēl (*CSCO,* XX, p. 26) soulignent qu'il s'agit d'une protestation collective du clergé tout en donnant la vedette à leur héros, même version dans le *gadla Āron Mankerāwi* (*CSCO,* XX, p. 126). Sur l'interprétation historique de cet épisode, voir Conti Rossini, *Il* Sēnodos *etiopico, Rendiconti dell'Accademia dei Lincei,* 1941, p. 47 et E. Cerulli, *Gli abbati di Dabra Libānos,* in *Orientalia,* XII, 1943, p. 236 et suiv.

[3] Selon la *Chronique de Ménélik II* de Guébré Sellassié, p. 40, n. 8, le Katatā est la région du mont Zeqwālā.

et fit prisonnier un certain Lālo au Ṭequrmeder[1]. Prisonnier signifiait esclave. La princesse indigente alla trouver Lālo, qui était devenu pâtre du troupeau royal, espérant qu'il lui donnerait du lait. Lālo lui fit manger de la polenta au beurre[2] : c'est de la polenta passée neuf fois de suite, de sorte qu'elle acquiert la consistance du sable.

Lālo en fit sa femme et elle lui donna quatre fils et trois filles. Les fils s'appelèrent Karayu, Tulamā, Mēčča et Wallo, les filles Alko, Durati et Ayāntu (*b*). Puis, *Aṣē* Amda Ṣeyon mourut et son fils Sayfa Are'ed lui succéda. C'est alors que les enfants de Lālo commencèrent à égorger le bétail des gens pour le manger. Le peuple s'assembla et cria justice. L'*azmāč* Endreyās manda alors à Lālo : « Je suis leur maître, comparais devant moi avec tes enfants ». Ayant reçu cet ordre, Lālo alla trouver Gabto, un sorcier qui invoquait un démon du Katatā nommé Waglyā. La mère de ce démon s'appelait Kurbit, son père était le premier de la race d'Adam[3]. Lālo demanda au sorcier : « Quel est le meilleur parti pour moi ? Il est bien vrai que mes fils ont égorgé le bétail de la population. Indique moi le moyen d'échapper à l'*azmāč* Endreyās ». Gabto lui répondit : « Amène sept taureaux beiges[4] (ou) sept blancs et le lait de sept vaches. Veille à ce que les vaches soient maigres et leurs veaux gras, car si les veaux sont maigres et les vaches grasses le lait risque d'être mauvais ». Lālo amena sept taureaux et le lait de sept vaches et demanda que faire. Gabto lui répondit : « Il y a trois démons appelés Waglyā[5], Yaminā (*c*), Fuçat. Je les attacherai à tes fils qui deviendront forts et invincibles. Quant à tes filles, je leur attacherai les démons appelés Atētē Ginbi, Atētē Harā et Atētē Dulā[6] ». Il leur fit boire le sang des sept taureaux et versa le lait des sept vaches dans le fleuve nommé Gallā (situé) entre le Dāwaro et le Katatā, il leur attacha les démons de ce fleuve et leur fit parler une langue étrangère, il leur fit dire *mālo mālo kotu kotu dāfi dāfi* (*d*)[7] et leur fit fumer la plante de *Seṭaṭirā*. Ils s'appelèrent Gallas, du nom du fleuve. Ensuite, ils trahirent leur maître et prirent son bétail. Les

(*b*) Tels sont les noms de ses enfants. Les quatre garçons causèrent du trouble en égorgeant le bétail de la population. Les pauvres s'assemblèrent et protestèrent auprès de l'*azmāč* Endreyās. Il se fâcha contre Lālu parce que ses fils égorgeaient le bétail. Lālu, à son tour, se fâcha contre ses fils, mais ceux-ci refusèrent de s'arrêter. Lālu, en difficulté, alla trouver Gabato, lui disant : « Mes fils ont égorgé le bétail, mon maître s'est fâché et a dit qu'il me tuerait et qu'il exterminerait mes fils. Que dois-je faire? » Gabato lui répondit...

(*c*) *Wamino.*

(*d*) *mālo gāllā, mālo gāllā.*

[1] Région s'étendant entre Ambo et Ǧibāt.

[2] Je traduis ainsi, faute de mieux, l'expression amharique *yaqebē nefro*. La signification magico-religieuse de ce mets semble confirmée plus bas (p. 137) puisque manger le *nefro* fait partie des coutumes païennes condamnées par l'auteur. Sur le *nefro*, voir J. Tubiana, dans *Rassegna di studi etiopici*, XIII, 1954, p. 85 et L. Ricci, *ibid.*, p. 87.

[3] Le nom d'Adam est connu des Gallas païens. Voir les textes cités par E. Cerulli, *Folk-Literature of the Galla of Southern Abyssinia*, in *Harvard African Studies*, III, 1922, p. 53, 140 et 152.

[4] Le mot galla *kormā* signifie « étalon » ou « taureau ». Ce dernier sens paraît s'imposer ici, le taureau étant l'animal de sacrifice (voir E. Cerulli, *Folk-Literature*, p. 176, l. 9 du texte cité).

[5] Dieu de fécondité des Gallas (voir G. W. B. Huntingford, *The Galla of Ethiopia*, in *Ethnographic Survey of Africa, North-Eastern Africa*, II, Londres, 1955, p. 76, d'après Krapf).

[6] Atētē est le nom de la grande déesse des Gallas (P. W. Schmidt, *Die Religion der Galla*, in *Annali Lateranensi*, I, 1937, p. 141; Beckingham, p. 76). Les trois variétés mentionnées ici font d'Atētē une divinité guerrière (*genbi* = amharique *gemb* « tour, mur », *harā*, galla « fatigue », *dulā* « lance, guerre, armée »). *Atētē Dulā* est la déesse qui assure la victoire aux Gallas. La croyance à la suprématie militaire des Gallas est demeurée ancrée en Éthiopie.

[7] Mots gallas : *mālo* « qu'est-ce que c'est ? »; *kotu* « viens », *dafi* « vite ».

